# ቀስተደመና ሬድዮ

## ትችት

## ግጭት ቅነሳ ወይስ ጦርነት ቅስቀሳ?

ወያኔና ሸአብያ ተስማምተው በሶስት የቅኝ ግዛት ውሎች ተመርኩዞ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የተከሰተውን ግጭት እንዲሸመግል ተሰይሞ የነበረው የዘሄጉ ኮሚሽን በእርግጥ በሁለቱ አገሮች መሃከል ሰላምን ያወርዳል፣ በአካባቢው መረጋጋትን ያሰፍናል ብ ሎ ያመነ ማንም ኢትዮጵያዊ ዴሞክራት አልነበረም። በነዚህ የቅኝ ግዛት ውሎች ተመር ኩዞ ሰጠሁ ያለው ውሳኔ ደግሞ እንኳዋን መረጋጋት ሊያመጣ ቀርቶ በቀጥታ የጦርነትና የትርምስ ግብዣ ሰነድ ሆኖ አግኝተነዋል።

ድሮም አይሰራም ነበር የምንለው ለምንድን ነው? ኮሚሽኑ ከጥንስሱ የነአቶ መለስ ዜናዊን «ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት» የሚል አጉል ቲወሪ ይዞ በመነሳቱና ይህንን ግ ጭት በቅኝ ግዛት ውሎች አማካኝነት እዳኛለሁ ብሎ እስከተግደረደረ ድረስ በኢትዮጵያና ኤርትራ መሃከል ያለው ችግር መሰረታዊ ምንነትና ምንጩን ለመረዳት የሚችልበት ምንም ተአምር አልነበረም። ከዚህ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ከሚል መንደርደሪያ ስለተነሳ ዛሬ የተከሰተውን የድንበር ግጭት በማንም ሁለት አገሮች መሃከል እንደተከሰተ ተራ ወይ ም «መደበኛ» (ክላሲካል) የድንበር ግጭት አድርጎ ወሰደ። በመሆኑም የአልጀርሱ ውል መሰረታዊ አላማዎች ሁለት ነበሩ። በአንድ በኩል ይህንን የድንበር ግጭት በማያሻማ ማካ ለል መፍታት። ሁለተኛ በአካባቢው ሰላም፣ መረጋጋትና ልማትን ለማስረገጥ በሁለቱ መን ግስታት መሃከል እርቅ ማውረድ። ሁለቱም የሚሰሩ አልነበሩም።

ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አልነበረችም። ሬፈራንደም ተደርጎ፣ ኤርትራ ነጻ ከወጣች አስር አመት እየሆነው ዛሬ ይህንን አንዳንዶች አልቆለታል የሚሉትን ጥያቄ ማን ሳት እንግዳ ነገር ሊመስል ይችላል። ነገር ግን የኤርትራ ሂደት የነጻነት ወይም የኢንዲፔን ዳንስ ሂደት ሳይሆን የመገንጠል ሂደት መሆኑን እስካልተቀበለ ድረስ ማንም ቢሆን እንኳዋ ን ለችግሩ መፍትሄ ሊያመጣ ቀርቶ ጥያቄው እንኳዋን እንደማይገባው ግልጽ ነው።

ኤርትራ በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ የቅኝ ግዛት አገላለጽ የጣልያን እንጂ የኢትዮጵያ ቅኝ ሆና አታውቅም። በመሆኑም የ1986 ሬፌራንደም ሊፈታቸው ያልቻለውና ያልፈታቸው ዞሮ ዞሮ በሆነ ምክንያት የወያኔና የሻብያ የፍቅር እፍታ ሲያልቅለት ህዝቦቻ ችንን ለመከራ የሚዳርጉ፣ ዞሮ ዞሮ ደግሞ በኤርትራም በኢትዮጵያም ህዝባቸውን የሚወክ ሉ መንግስታት እስኪመጡ ድረስ መፍትሄ ሊያገኙ ከቶም የማይችሉ ሁለት መሰረታዊ ች ግሮች ነበሩ። ላይ ላዩን አስገራሚ ቢመስልም የተከሰቱት ችግሮች በአንድ በኩል ከኤርት ራ መገንጠል ጋር የተያያዙ ናቸው። እዛው በዛው ደግሞ «ወተቴንም አልለቅ ጥጃዬም አ ይከሳ» በሚል የአጉል ብልጣ ብልጥ ዘይቤ የሻብያ መንግስት የመገንጠልን መዘዝ ለመቀበ ል አቅቶት «ነገሮች እንደዱሮው» ይቀጥሉ ከማለቱ የመነጩ ችግሮች ነበሩ።

መገንጠል የፈጠራቸው ችግሮች ምንድን ናቸው? ግልጽ ነው። በኤርትራና ኢትዮጵ የአ መካከል የነበረው ግንኙነት ባንጎላና በፖርቱጋል የነበረው ግንኙነት አይነት አልነበረም ። የኤርትራ «ነጻነት» ሂደት በዝች አገር ከሚገኙት ዘጠኝ ብሄረሰቦች አራቱ (ማለትም ት ግራይ፣ አፋር፣ ኩናማና ሳሆ) አብዛኛውን የብሄራቸውን ክፍል (ማጆሪቲውን) ከድንበር ባሻ ገር ትተው የተከፈሉበት ሂደት ነው። የኤርትራ ሬፈራንደም ይህንን ችግር ፈጠረው እንጂ አልፈታውም።

የሸአብያ አልገነጠልም ባይነት የፈጠራቸውስ ችግሮች ምንድን ናቸው? እነዚህንም ሁላችንም እናውቃቸዋለን። በፖለቲካ ነጻ አገር። በኢኮኖሚ ግን አንድ አገር ሆኖ የመቀ ጠል ብቻ ሳይሆን እንዲያውም በቀድሞዋ ቅኝ ገዝ ተብየ አገር ከቀድሞው በተሻለ የፖለ ቲካና በተለይም ደግሞ የኢኮኖሚ ጥቅምን የማረጋገጥ ህልም ያመጣቸው ችግሮች ናቸው። ህልሙ ለጥቂት አመታት ሰራ። በዚህ «አልሸሹም ዘወር አሉ» አይነቱ የሸአብያ የመገን ጠል ሂደት በሁለቱ አገሮች መሃከል ያለው «መንግስት ከመንግስት» ግንኙነት ሙሉ በሙ ሉ ለኤርትራ እንደሚያደላ ተደርጎ በመበጀቱ ብዙ ኢትዮጵያውያንን አስቆጣ። በራሱ በወ

ያኔ ውስጥ ኤርትራ ነጻ ወጥታለች ራሱዋን ትቻል፣ ኤርትራ ከእንግዲህ እንደማንኛውም ባእድ አገር መቆጠር አለባት የሚሉ ሃይሎች አየሉ። ሸአብያ ኢትዮጵያን እንደተወረረ አገር መቆጣጠሩ ተገታ። አሻፈረኝ በማለት የመገንጠሉን መዘዝ አልቀበልም ብሎ «በድንበር ሰበብ» ጦር መዘዘ። ከዚያ የሆነውን እናውቀዋለን። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን የድንበሩ ኮሚሽን ምንም ይወስን ምንም ከነዚህ የሸአብያ መገንጠል/አለመገንጠል የተምታታ ሂደት የፈለቁትን ችግሮች የሚፈታ አልነበረም።

______ድንበሩን መቶ በመቶ እንዳለ ቢተወውና ከግጭቱ በፊት በነበረው ይርጋ ቢል ከዚህ ግጭት ሰባት አመታት በፊት የኤርትራ የመገንጠል ሂደት ለአፋሮችና ለሌሎች ህዝቦች ያስከተለውን መዘዝ እንዳለ ይተዋል እንጂ ለአካባቢው ሰላምና መረጋጋት ምንም የሚያደርገው አስተዋጽኦ አልነበረውም። በሌላ በኩል ደግሞ ድንበሩን በቅኝ ግዛት ውሎች መሰረት አስተካክላለሁ የሚልበት ሌላ አማራጭ ነበረው። ይኸም ሌሎችን በቅኝ ግዛቱ ዘመን እንኳዋን ያልተነኩ ህዝቦችን መልሶ ከመከፋፈልና ከማተረማማስ ሌላ ምንም ነገር ሊያመጣ ስለማይችል የኤርትራ መገንጠል በፈጠረው ችግር ላይ ሌላ ተጨማሪ ችግር መፍጠር እንደሚሆን ግልጽ ነበር። በአልጀርሱ ውል መሰረት አለም አቀፍ ኮሙኒቲ ተብየው ነገር ከተንቀሳቀሰባቸው ሁለት ዋና ዋና አላማዎች አንዱ (ማለትም የድንበር ማካለሉ አላማ) በዚሁ ተሸኘ ማለት ነው።

ሁለተኛው አላማ ደግሞ በሁለቱ መንግስታት መሃከል እርቅ የማውረዱ አላማና በዚህ አማካኝነት በአካባቢው ሰላምን መረጋጋትንና ልማትን የማስፈን አላማ ነበር። አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ይህንን አጉል አላማ ሲያሳድድ ዋናውን ጥያቄ ልብ ያለው አይመስልም። ይህ ዋናው ጥያቄ ምንድን ነው? ባካባቢያችን ዋናው ችግር ወያኔንና ሸአብያን ማስታረቅ ሳይሆን እነዚህ ሁለት ጸረ ህዝብ ሃይሎች ከየህብረተሰባቸው ጋር እርቅ እንዲያደርጉ፣ በሁለቱም አገሮች ዴሞክራሲየአዊ ሁኔታ እንዲጎለብት የማገዝ ጥያቄ ነው። ይህ ካልሆነ ሸአብያንና ወያኔን ማስታረቁ ለአካባቢው ሰላምና ዴሞክራሲ ብቻውን ምንም የሚያመጣው ነገር የለም።

ከፍ ብለን ድንበሩን እንዳለ ቢተውትም፣ ቢያንቀሳቀስትም ችግር ነው እንዳልነው ሁሉ የኤርትራም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ በሚገባ እንደሚያውቀው ይኸ የወያኔ/ሸአብያ ዝምድናም ጉዳይ በየትኛውም ገጽታው ቢወሰድ አስቸጋሪ ነው።

ወያኔና ሸአብያ ሲጣሉና ሲኩዋረፉ የሚከተለውን መዘዝ ሁለቱም ህዝቦች ከመቶሽህ በላይ ልጆቻቸውን በሰውበት፣ ሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ለስደትና ለመፈናቀል በተዳረጉበት፣ አርሶ አደሮችና ሰርቶ አደሮች የአለም አቀፍ በጎ አድራጊዎችን እጅ እያዩ ለመኖር በሚገደዱበት፣ ነጋዴዎችና ባለሃብቶች ከሞቀ ከተደላደለ ኑሮዋቸው በዘፈቀደ ተባርረው ለችግር በተዳረጉበት የድንበር ጦርነት ተብየ ነገር አይተነዋል።

ወያኔና ሻብያ ችግር የሚፈጥሩት ሲጣሉ ብቻ አይደለም። ሲፋቀሩም እንዲሁ አስቸጋሪ የሆኑ ጸረ ህዝብ ሃይሎች ናቸው። ይህንን ደግሞ በተለይ የኢትዮጵያ ህዝብ ከድንበር ግጭቱ በቀደሙት ሰባት አመታት ይህ አፍላ ፍቅር ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት ገፈቱን ቀምሶት ስለሚያውቀው እርቃቸውንም እስከዚህ የሚመኘው አይደለም። አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ሲጣሉ ወደጦርነት ይማግዱኛል፣ ሲፋቀሩ ደግሞ ተጋግዘው ያፍኑኛል ብሎ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚታገላቸውን መንታ ሃይሎች የማስታረቁን ጉዳይ እንደዋና አጀንዳ ይዞ እስከተንቀሳቀሰ ድረስ ልክ እንደድንበር ማካለሉ በዚህም በኩል ለሰላምና ለመረጋጋት የሚያግዝ እርምጃ ሊወስድ እንደማይችል ግልጽ ነበር።

ከዚህ ሁሉ አንጻር ሲታይ ከሄጉ ውሳኔ ለሰላም የሚጠበቅ ምንም በጎ ነገር አልነበረም። አልመጣምም። የባሰ አለ። ግጭት ቅነሳ ያልተሳካለት ኮሚሽን ውሳኔ ከተፈራው በላይ ለሰላም አደገኛ ውሳኔ ሆኖ አግኝተነዋል። አርእስታችን ላይ ጦርነት ቅስቀሳ ያልነውም ለዚህ ነው። እንዴት? ለምን? ይህንን በሚቀጥለው ሳምንት ለመተንተን እንሞክራለን።

30/04/2002